[illegible]
[illegible]

[illegible]

9/9/92

[illegible]

[illegible]

# አብርሃም
# የእግዚአብሔር ወዳጅ

**በሽፈራው ወልደሚካኤል**

**ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን**

**አዲስ አበባ**
**1989 ዓ.ም**

**አሳታሚ:- ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ**
**ሥነ-ጽሑፍ ክፍል**

# መታሰቢያ

አባታችን አቶ ወልደሚካኤል አብሴ እኛን ወንዶች ልጆቻቸውን ከብት እያሰጠበቁና እያሳረሱ ሊኖሩ ሲችሉ የኛን ጥቅም ከራሳቸው ጥቅም በማስበለጥና በማስቀደም ከገጠር ወደ ከተማ በመውሰድ እንድንማር ስላደረጉን፣ እናታችን ወ/ሮ አቻሜለሽ ዳምጤ ትጋትን፣ ታታሪነትን፣ ትህትናንና ፈሪሀ እግዚአብሔርን በቃልና በሕይወት እኔን፣ ወንድሞቼንና እህቶችን ስላስተማሩን ይህችን መጽሐፍ በፍቅርና በአክብሮት ማስታወሻ አድርጌላቸዋለሁ።■

# ማውጫ


ገጽ

መግቢያ ........................................ 4

ምዕራፍ 1
የአብርሃም የዘር ግንድና ጥሪ ........................................ 6

ምዕራፍ 2
ለአብርሃም የተሰጡ የቃል ኪዳን ተስፋዎች ........................................ 24

ምዕራፍ 3
አብርሃምና ሣራ ........................................ 42

ምዕራፍ 4
አብርሃምና ይስሐቅ ........................................ 57

ምዕራፍ 5
አብርሃምና ሎጥ ........................................ 88

ምዕራፍ 6
የአብርሃም ፈተና ........................................ 99

ምዕራፍ 7
የአብርሃም የአምልኮ ሁኔታዎች ........................................ 108

# መግቢያ

እግዚአብሔር በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን ስም ለውጧል። ስማቸው ከተለወጠላቸው ሰዎች መካከል አንዱና በኋላም "ወዳጄ" ብሎ የጠራው አብርሃም ነው።

"አብርሃም" የሚያስቀና፣ የሚያሳዝን፣ የሚያናድድም ሕይወት ያሳለፈ ሰው ነው። ሕይወቱ፥ የቤተሰቡም ሕይወት ሳይቀር ብዙ ኮረኮንች መንገድ ያለፈ፥ ተራራ የወጣ፥ ቁልቁለት የወረደ ነው። ብዙም ግራ መጋባት የነበረበት ነው። የአብራም ሕይወት የእግዚአብሔር ተስፋ በሞላበት አእምሮና ልብ ምትክ ተስፋ ማጣትና መዋዠቅ የተንሰራፋበት ሕይወት ነው። የማይታየው አምላክ፥ ማለትም በማስረጃ ተይዞ ሊቀርብ የማይቻለው አምላክ ተስፋ ወደ ክርክር፥ መላ ምትና መፍትሔ ፍለጋ የተካሄደበት ሕይወት ነው። ፍዳ ያሳየ፥ በሀሳብ ተራራ ያስቧጠጠ፥ ቆንጥር ለቆንጥር ያንከራተተ በሞትና በሕይወት መካከል ያለውን ድንበር ለመለየት እንኳን እስኪያቅት ድረስ ሰልፍ ያለፈበት ሕይወት ነው። የተሰማው እንዳልተሰማ፥ የታየው እንዳልታየ የሚያስቆጥር ጥርጥር በግል ሕይወቱ ከዚያም አልፎ በመላ ቤተሰቡ ውስጥ ያለገደብ የነገሰበት ሕይወት ነው። ሲጽፉትና ሲተርኩት ቅልብጭ ይላል፤ ይህን ሕይወት ለኖረው ለአብርሃም ግን በጣም ረጅምና ትዕግሥት አስጨራሽ ነበር። ጌታ አምላክ የአንዳንድ ሰዎችን ሕይወት የፈቃዱ፥ የድንቅ አሠራሩና የአካሄዱ ማስተማሪያ መሣሪያ፥ መጻፊያ ቀለም ያደርጋል። አብርሃም ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ነው ብዬ አምናለሁ።

ሰውን ለማወቅ አንዱና በጣም ጠቃሚው መንገድ ቢቻል አብሮ፣ ባይቻል ደግሞ በቅርቡ መኖር ነው። አብርሃምን እናውቅና ከዚህ ታላቅ ሰው ሕይወትና ከቤተሰቡ

አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ... ያድርግብኝ" የሚል ነበር። (ሩት 1፥16–17)

ሩት ጅምሯን መፈጸም ብቻ ሳይሆን የንጉሥ ዳዊት ዘር ግንድ ተጠቃሽ ለመሆንም በቃች። የዖርፋ የሕይወት ጉዞ ታሪክ ግን ሳይጠናቀቅ እመለየቷ ላይ ቆመ።

በጅምር ስለቀሩ ሁኔታዎችና ዓላማዎች በአዲስ ኪዳንም ብዙ ተጽፏል። ከእነዚህም ውስጥ በማቴዎስ 25 የተጠቀሰው የአምስቱ ቆነጃጅት ታሪክ አንዱ አሳዛኝ ታሪክ ነው።

አሥር ሆነው ሙሽራውን ለመቀበል ተመረጡ። ተዘጋጁም። መብራት ለመያዝም ተመረጡ። ሙሽራውም እንደተጠበቀው መጣ። ይሁን እንጂ ሙሽራው በመጣ ጊዜ ግን አምስቱ ከደስታው ተካፋይ ለመሆን አልቻሉም። ለመብራታቸው የሚያስፈልገውን ዘይት አልያዙም ነበርና። ጥሩ ጅምር ግን ከጅምር ያላለፈ ጅምር።





በማቴ.19፥16–22 የተመለከተውም የሐብታሙ ወጣት ታሪክ ከዚህ የተለየ አይደለም። የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በጉጉት ጀመረ። ወደ ጌታ ኢየሱስ፥ ወደ እውነተኛው የሕይወት መንገድ ሄደ። ትክክለኛውንም ጥያቄ ጠየቀ። ሆኖም የዘላለምን ሕይወት ሳያገኝ እንደተሰናከለና በጅምር እንደቀረ ታሪኩ ያስረዳል።

ከጳውሎስ ጋር በመልካም ጀምሮ ፍፃሜው ሳያምርለት የቀረው ዴማስም ለዚህ ርዕስ እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል። (2ጢሞ.4፥10)

ከግብ ሳይደርስ እንከን ስላጋጠመው ጅምር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን ጽፏል፤ "የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር። ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማነው? ... በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን?" (ገላ.3፥1–3)

ጌታ ለዘላለም ደህንነት የጠራህ ወገኔ እስቲ ለአንድ አፍታ አንተነትህን ተመልከተውና ከህሊናህ ተመካከር። ከጌታ ጋር ስለጀመርከው ሕይወት ለአምላክህ የገባኸውን ልዩ ልዩ ተስፋና ቃል ኪዳን በእውነት ፈጽመሃልን? ጌታ እነዚህን ሁሉ መዝኖ "... ወዴት ነህ?" ቢልህ መልስህ ምን ይሆን?

## የኢየሱስና የጳውሎሲ ምሣሌነት፤

ጅምራቸውን እግዚአብሔርን በሚያስከብር ሰውን በሚጠቅም መንገድ የፈጸሙ አያሌ ምስክሮች አሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና ሐዋርያው ጳውሎስን ብቻ በጥቂቱ እንመለከታለን።

ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው" በማለት ለምን እንደመጣ ግቡም ምንና እስከምን ድረስ እንደሆነ ግልፅ አድርጎ አስታወቃቸው። በተግባር ሲታይ ግን እንደቀላል የሚያልፈው ጉዳና አልነበረም። ስለዚህም ተንበርክኮ "አባት ሆይ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ" እያለ ይጸልይ ነበር። "... በፍርሃትም" ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ይንጠባጠብ ነበር።" (ሉቃስ 22፥42–45) የሚለው ቃል ጌታ ኢየሱስ ጅምሩን ለመፈጸም በምን ዓይነት ጭንቅ እንዳለፈ ያስረዳናል።

የሁኔታው መከፋትና መክበድ ጌታ የጀመረውን እንዳይፈፅም አገደውን? አላገደውም። ጌታ ሞትን ለዚያውም የመስቀል ሞትን እስከመቀበል ደረሰ። የመጨረሻ የመስቀል ቃሉም "ተፈጸመ" የሚል መሆኑን ሐዋርያው ዮሐንስ ዘግቦታል። (ዮሐ.19፥30)

በዚህ አንፃር በምሳሌነት የሚያበራ ሕይወት ያለው ሌላው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ የመጀመሪያው ተንከራታች ሰባኪና ሚስዮናዊ ነበር ለማለት ይቻላል። ይህም ሰው "በመስዋዕትነት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሰዋልና የምሄድበትም ጊዜ ደርሷል፤ መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫውን ጨርሻለሁ ኃይማኖትን ጠብቄአለሁ።" በማለት ተልእኮው ጫፍ ማድረሱን በእርግጠኝነት አብስሯል። እኛም የዚህ ዘመን ክርስቲያኖች የእምነታችንን ጀማሪና ፈጻሚውን ስናይ ጌታ ያስጀመረንን ያስጨርሰናል።፤ ቅዱስ ቃሉ እንደሚል "በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቻለሁና።" (ፊልጵ.1፥6) "እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም።" አሜን!



የጅማሬንና የፍጻሜን ነገር ይህን ያህል ከአየን ወደተነሳንበት አብይ ጉዳይ እንመለሳለን።

የአብራም የትውልድ ሥፍራ የከለዳውያን (ባቢሎናውያን) አገር የሆነው ዑር ነው። ከዚያም በአባቱ በታራ ውሣኔ ከመላ ቤተሰቡ ጋር አባቱን አጅቦ ከዑር ወደ ከንዓን ለመሄድ ተነስቶ ካሰበበት ግብ ሳይደርስ በካራን ተቀመጠ። በካራንና በከነዓን መካከል በጣም ረጅም መንገድ ይቀር ነበር። በዚያም ማለትም በካራን የአብራም አባት ታራ ሞተ። ከዚያ በፊት ታይቶና በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ የማያውቅ የእግዚአብሔር ጥሪ መጥቶ በአገር እስኪያወጣው ድረስ አብራም በካራን ኖረ። ለመሆኑ በመንፈሳዊ ሕይወት ረገድ ስንቶች ነን ለከነዓን ታጭተን በካራን የቀረን? ወንድሜና እህቴ ከነዓን ሳንደርስ በካራን እንሙት። ይህ የሰነፍ ሞት ነውና።

አብራም በካራን እያለ ልዩ ነገር ወደ ሕይወቱ መጣ። በፊት በአባቱ ውሣኔ የትውልድ አገሩን ለቅቆ ወደ ካራን መጣ። አሁን ደግሞ በታላቁ አምላክ ትዕዛዝና ውሣኔ ወደ ሌላ ቦታ እንዲንቀሳቀስ ተጠየቀ። በራስ አለማደር እራስን የማስተዳደሩን መብት ለሌላ መስጠት መሰል ነገሮችን ሊያስከትል እንደሚችል ይህ ታሪክ ያስገነዝበን ይሆን? "ከአገርህ፥ ከዘመዶችህ፥ ከአባትህ ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ" የሚል ትዕዛዝ እንደ ደረሰው፤ በዚህ ትዕዛዝ መሠረት አብራም ከካራን ወደ ከነዓን ሄደ።

በከነዓን ምድርም ወደ ሴኬም በኋላም ወደ ቤቴል ከዚያም ወደ አዜብ ሄዶ መኖር ጀመረ። በአገሩም በደረሰው ራብ ምክንያት ወደ ግብፅ ምድር ሄደ። ከዚያም ከግብፅ ተመልሶ በቤቴል መኖር ጀመረ። በቤቴልም እጅግ በለጸገ፤ ከመንጋዎቻቸው ብዛት የተነሳ በርሱና በወንድሙ ልጅ በሎጥ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ። በዚህም ምክንያት በአብራምና በሎጥ መካከል የመሬት መከፋፈል መደረግ ነበረበትና ይህንኑ አደረጉ።

የአብራም ሚስት ሦራ መካን ነበረች። ስለዚህም ለብዙ ዓመታት በቤ ውስጥ የሕፃን ድምፅ ባዕድና፥ የማይታወቅ፥ በአንፃሩ ደግሞ በትልቅ የሚጠበቅ ተስፋ ነበር። ይሁን እንጂ የአብራምና የሦራ ቤት በልጅ የመጠራት፥ ስማቸውን ለትውልድ የማስተላለፍና ሀብታቸውን ለሚ የማውረስ ዕድል የሌለው ቤት ነበር። ከዚህም የተነሳ ባልና ሚስቱ ተማከ ተስማምተው ልጅ ከገረዳቸው ከአጋር ልጅ እንዲገኝ ሆኗል። በእስማኤል ጊዜ የአብራም ዕድሜ 86 ዓመት ያህል ነበር።

አብራም 100 ዓመት ሲሞላውና ሦራ የ89 ዓመት ሲሆናት ስ በእግዚአብሔር ተለወጠ። አብራም አብርሃም ተባለ። ሦራም ስሟ ተለውጦ ተባለች። አብርሃምና ሣራ ስማቸው ከተለወጠ በኋላ ይስሐቅን ወለዱ። ብ ሳይቆይ አብርሃም ልጁን ይስሐቅን መስዋዕት እንዲያደርግ በእግዚአብ ተጠየቀ። አብርሃምም ትእዛዙን ለመፈጸም እርምጃዎች ቢወስድም እግዚአብ ልጁን አተረፈለት። አብርሃም የ137 ዓመት ሽማግሌ በነበረበት ጊዜ ሚስቱ ሞተች።

አብርሃም ሣራን ከቀበረ በኋላ ኬጡራ የተባለች ሚስት አግብቶ 6 ል ማለትም ዘምራንን፥ ዮቅሳንን፥ ሜዳንን፥ ምድያምን፥ የስቦቅን፥ ስዌሕን የተባ ልጆች ከተወለዱለት በኋላ በ175 ዓመቱ አንቀላፋ።





አልረባ ነገር ይጥለዋል። የእግዚአብሔር አመራረጥ ግን ተቃራኒውን ይከተላል ማለት ይቻላል። የተናቀውን ይወስድና በተናቀው ውስጥ ሆኖ ጀግና ያደርጋል፤ አዋቂ ያደርጋል፥ ተፈላጊ ያደርጋል፥ ይገለገልበታል፥ የከበረ ያደርጋል፥ ይከብርበታልም።

ከላይ እንደተመለከትነው አብርሃም አገር፥ ወገንና ቤት የነበረው ሰው ሲሆን የተጠራው ከአገሩ ከወገኑ ከቤቱ እንዲለይ ነበር። ከለመደው አገርና ቀዬው፥ ከሚወዳቸውና ከሚወዱት ወገኖቹ፥ ከሚያውቁትና ከሚያውቃቸው፥ ቋንቋቸውና ቋንቋው፥ ባህላቸውና ባህሉ፥ መልካቸውና መልኩ ከሆኑ ወገኖቹ፥ ጉረቤቶቹ ከተደራጀና ከሞቀ ቤቱ እንዲወጣ ተጠራ። ጀርባውን ለሚያውቀውና ለሚወደው፥ ፊቱን ደግሞ የራሱን፥ የቤተሰቡንና ምናልባትም ልጆች የሚኖሩት ቢሆን የእነርሱንም "ነገ" ወይም የወደፊት ዕድል ፈንታ ለማያውቀው ሰጥቶ እንዲጓዝ የተጠራ ሰው ነው። የታወቀን፥ የተጨበጠን፥ በእጁ ያለን ነገር አራግፎ በተስፋ ብቻ ታምኖ እንዲሄድ የተጠራ ነበር።

አብርሃም ተጠራ፥ ጌታን ታዘዘ ማለቱ የበለጠ ይቀላል። ታዛዥ እንጂ ሥር ነቅሎ የሚሄድበት አገር ለም ይሁን ጠፍ፥ ቀዝቃዛ ይሁን ሞቃት ሳይለይ፣ ሕዝብ ይኑረው አይኑረው፥ ፍቅር ይጠብቀው ጥል ሳያውቅ በእጁ ያለውን፥ የጨበጠውን ጥሎ መሄድ... ውድ አንባቢ ሆይ፥ እጅግ በጣም ከባድ አይደለምን? አንዳንዴ የስንት ሰው ፊት ታይቶበት፣ ስንት ገንዘብ ወጥቶበት፣ የተገኘን ውጭ አገር የመሄድን ዕድል ከአጋጠመ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ሲለያዩ ብዙ ወገኖቻችን የሚሆኑትን ሁኔታ አይቻለሁ፤ እመሰክራለሁ። ቦሌ አስፋልት ባይሆን ውኃ ሳያሻው በእንባ ብቻ ሣር በበቀለበት ነበር ብል ማጋነን አይሆንም። ለመለየት ሥነ ልቡናዊ ውሳኔ ማድረግ ራሱን የቻለ ፈተና ነው። ጨጓራ የሚልጥ፥ እንቅልፍ የሚነሳ፥ ግራ የሚያጋባ ነው። ሌላው አድካሚ ነገር የቤት ቅራቅንቦ ማዘጋጀቱ፥ የሚሄደውንና የሚቀረውን፥ የሚያዘውን የሚተወውን መለየቱ፥ ስንቅ መሰነቁ፥ በቀላሉ



የማይታይ ጉዳይ ነው። አዲስ አበቦች፥ ሶደሬ እንኳ ሲሆዱ የዕቃቸው አበዛዝ! ጎልያድ በሕይወት እያለ የእስራኤል ጀግና ሁሉ ጭብጥ አልሞላ ብሎ ተሸማቆ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አመልክቶ "ሳኦልና እስራኤል ሁሉ እንዲህ የሚላቸውን የፍልስጥኤማውያንን ቃል በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ ደነገጡም" ይላል። ድል ከተደረገ በኋላ ግን ጎልያድ ትንሽ ያውም ዝንብ ጭምር የሚፈነጭበት ይሆናል። ከዚያ በፊት ግን እርሱን መግጠም፣ ፊቱ መቆምና መፋለም ብዙ ያንቀራጥጣል፥ ያስምጣል፥ በጣም ያንገላታል። ብርቱ ውሳኔና ጀግንነትን ይጠይቃል።

በሌላ በኩል አብርሃም ጥሎት እንዲሄድ የተጠየቀው አገርና ሁኔታ የዓለም ምሳሌ፤ የግብፅ ምሳሌ ነው። እንዲኖርም የተጋበዘበት አዲስ ሕይወት ደግሞ የመናኝ፥ የቅድስና ሕይወት ምሳሌ ነው። ልብን አጣብቀው የሚይዙ፣ አንገትን ወደ ኋላና ወደ ቀድሞ ነገር የሚቆለምሙ ትዝታዎች፥ በጆሮ ውስጥ የሚደውሉ ብዙ ድምጾች፥ አውታሮች፥ ጊዜና ባሕል የገመዳቸው ጉታች ገመዶች አሉ። ይህንን መለየት ደግሞ ከባድ ነው። ግን ልዑል እግዚአብሔር ካዘዘ የሚበጀው መታዘዝ ብቻ ነው።

የተጠራንበት ፍቅርም ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ እንጂ በታች አይደለም—አይሆንምም። ውሱን ሃሳቦች ወደ ታች ጎትተው ሊያስቀሩት የሚችሉም አይደለም። የውድድር ሯጭ የሚከብደውን ሁሉ እያወለቀ በመጣል ከአሸናፊነት ሊያስቀሩት የሚችሉም ነገሮች ሁሉ እንደሚጥል እንዲሁ ለዚህ ፍቅር የተሰለፈ ሯጭ ወደ ኋላ ሊይዙ የሚችሉትን በርሱ ላይ ያሉትን አጓጉል ሸክሞች ሁሉ በመጣል ለተጠራበት ፍቅር በድል አድራጊነት ይገሰግሳል። ብዙ ምኞቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነኚህም ወደ ጎን ይባላሉ፤ የሚቀረው በልብ ያለው ፍቅር ብቻ ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ክርስቲያን በጣም የሚወደውንና ምርጫው የሆነውን ነገር እንዲተው



# ምዕራፍ 2

## ለአብርሃም የተሰጡ የቃል ኪዳን ተስፋዎች

ልዑል እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ትዕዛዝ ሰውና ዘመድ አልባ የሚያደርገው የሚያስመስለው ቢሆንም በምትኩ ግን በአያሌና ዘላለማዊ በሆኑ ቃል ኪዳኖችና ተስፋዎች ሲጠቀልለው እናስተውላለን። እነዚህ ተስፋዎች በዘፍ.12፥1–3 ተዘርዝረዋል። "እግዚአብሔርም አብራምን አለው:- ከአገርህ፥ ከዘመዶችህ፥ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።"

ተስፋዎቹን እንደሚከተለው መተንተን ይቻላል፤

ሀ. ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤

ለ. እባርክሃለሁ፤

ሐ. የሚባርኩህን እባርካለሁ፤

መ. የሚረግሙህን እረግማለሁ እና

ሠ. የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፤

ከእነዚህ በተጨማሪ ርስት (አገር) እንደሚሰጠው ተስፋ የተገባለት መሆኑን በዘፍ.12፥1 እና ዘፍ.15፥5 ለመረዳት ይቻላል።

ወደ ተስፋዎቹ ገለጻ ከመግባታችን በፊት ስለ እግዚአብሔር ተስፋ ባሕርያት አንዳንድ ነጥቦች ማስታወሱ ጠቃሚ ይሆናል።

ስለ እግዚአብሔር ተስፋ ስናስብ አንዱ ልንገነዘበው የሚገባን ከተሰጠው ተስፋ ጀርባ ለሥልጣኑ ዳር ድንበር፥ ለኃይሉ ገደብ የሌለው እግዚአብሔር አምላክ የሚቆም መሆኑን ነው። ስለዚህ ሁኔታ "እግዚአብሔር የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንደሚችል አጥብቆ እየተረዳ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም" በማለት በሮሜ 4፥21 ተመዝግቧል።

ኃይልና ሥልጣኑ ከመጠን ይልቅ የበዛው፣ በሚዛንም የማይለካው ሕያው አምላክ ከሚሰጠው ተስፋ ጀርባ ሁልጊዜም ለዘለዓለም ይቆማል።

"እኛ እምናምነው ግዑዝ አይደለም፣

በየምክንያቱ መልኩ አይቀየርም፣

ያው ነው አሁንም ያው ነው ዘላለም፣

አልፋ ኦሜጋ ሕያው ነው በዓለም"

ሌላው የእግዚአብሔር ተስፋ ባሕርይ የማይቀር፥ የማይሻር፥ (በአገራችን ከቅርብ ዓመታት በፊት እንሰማ የነበረውን አባባል ልዋስና) ለምንም ለማንም የማይበገር መሆኑ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሰለሞን ሲመሰክር "እንደተናገረው ተስፋ ሁሉ ለሕዝቡ



ለእስራኤል ዕረፍትን የሰጠ እግዚአብሔር ይመስገን፤ በባሪያው በሙሴ ከሰጠው ከመልካም ተስፋው ሁሉ አንድ ቃል አልወደቀም" ብሏል። (1ነገ.8፥56)

የእግዚአብሔር ተስፋ ግብ "ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጠን፣ ከመለኮት ባሕርይ በተስፋ ቃል ተካፋዮች እንድንሆን" ማድረግ ነው። (2ኛጴጥ.1፥4)

እነዚህ ተስፋዎች በምትክ የተሰጡ መሆናቸውን መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል። አብርሃም እነኚህን ያገኝና ይይዝ ዘንድ እጁ፥ እሱነቱ ባዶ መሆን ነበረበት። አብርሃም ተስፋ የተሰጠው በእጁ ያሉትን የእኔ የሚላቸውን ምናልባትም በሰው አስተሳሰብ መለኪያ የሌላቸውን ነገሮች እንዲተው ተጠይቆ ነው። እነዚህም:-

ሀ. አገር

ለ. ዘመድ

ሐ. የአባት ቤት

እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው። ይህንንም እራሱ በቃሉ ይናገራል። (ዘፀ.2፥6) እግዚአብሔር አንድን ሰው ሊጠቀም ሲፈልግ ያንን ሕይወት እርቃን የማስቀረት ባህርይ አለው። ማለትም ያ ሰው እንዲተዋቸው የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ። ይህንን በአብርሃም ሕይወት ብቻ ሳይሆን በዮሴፍና በጳውሎስም ሕይወት በጣም ግልጽ ሆኖ እናየዋለን። እስቲ እነኚህን አብርሃም እንዲተዋቸው የተጠየቃቸውን ነገሮች እናጢንና ለሕይወታችን የሚቀርልንን ትምህርት ነገር እስቲ እንመልከት።

አይሆንም። እግዚአብሔር ባስቻለን መጠን ግን ክርስቶስን በማያከብር ልማዳቸው አንተባበራቸውም – እንለያቸዋለን እንጂ።

ነገር ግን ምርጫ የማድረግ ነገር ከመጣ ምርጫችን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሆን አለበት። በከፊል ከሙሴ ሕይወት ይህን እናያለን:-

"ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት የንጉሥንም አዋጅ አልፈሩም። ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና።" (ዕብ.11፥23–27)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከጸለየው ታላቅና ረጅም ጸሎት ይህን እንማራለን።

"ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና እንዲህ አለ:- አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው።"

"... ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው። የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው፤ ቃልህንም ጠብቀዋል። የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን ያውቃሉ፤ የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፣ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላከኸኝ አመኑ። እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤ የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፣ እኔም ስለ እነርሱ ከብሬአለሁ። ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው። ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅኋቸውም መጽሐፉም እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።"

"... እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላከኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል። አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።" ዮሐ.17፥1–2፤ 6–11፤22–23)

ከእነዚህ ጥቅሶች አንድ ክርስቲያን አገሩ፣ ዘሩ፣ ቋንቋው ምንም ይሁን ከሌላው ክርስቲያን ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት እንማራለን። ጌታ ኢየሱስ ልጆቹ "አንድ" ማለትም እርስ በእርሳችን በጣም ቅርብ እንድንሆን ይፈልጋል። የአንድነቱና የቅርብነቱ መመዘኛ ወይም ምሳሌ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ መካከል ያለው ግንኙነት ነው። ይህንን "... እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው ... እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ..." (ዮሐ.17፥11፣22) ከሚሉት ቃላት በግልፅ እንረዳለን።

ወገኖች እግዚአብሔር አሁንም ቃሉን አልለወጠም። ሀሳቡን አልቀየረም። እንደአብርሃምና እንደ ሙሴ ጊዜ እንደነበረ አሁንም ያው ነው። መውጣትና

መለየት ጌታ ኢየሱስ በደሙ ከዋጃቸው ልጆቹ ጋር አንድ እንድንሆን የሚጠየቅብን መሠረታዊና ዋነኛ እርምጃ ነው።

ወገኖች:-

ዘመናችን በአካባቢ በዘርና በጎሳ መሰባሰብን የጊዜው መርህ አድርጎ የወሰደው ይመስላል። በጌታ ልጆች መካከል ግን ይህ የተከበረ ቦታ ሊሰጠው አይገባም። ይህን ሀሳብ ከገላትያ ጥቅሶች በመውሰድ ልደምድመው:-

"በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።፥ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።" (ገላ.3፥26-29) አብርሃም በእግዚአብሔር ከታዘዛቸው ትዕዛዛት ውስጥ አንዱም እንኳን ቀላልና ግድ የለም የሚባል አልነበረም። አብርሃም አገሩን እንዲተው ተጠይቋል፥ ታዟል። ሰው አገር የሚያስጥልና የሚያስተው ሁኔታ ሲፈጠርበት በሐዘንና በትካዜ ያደርገዋል እንጂ በሳቅና በደስታ አይደለም። አገር መተኪያ የላትምና። እንኳን አገርና ለእስራኤላውያን ጊዜያዊ ማረፊያ የነበረችው አገራቸው ያልነበረችው ግብፅ በሕዝቡ ልብና አእምሮ ብዙ ትዝታ መጣሏ የማይረሳ ነው።

ሌላው አብርሃም እንዲተው የተጠየቀው ዘመድ ነው። የሥጋ ዘመድ የሌለው ሰው በተላጠ ግንድ ይመሰላል። በልምድ እንዳየሁት በየሕብረተሰቡ ወዳጅ ዘመድ



ለመፍጠር ብዙ መፍጨርጨር ይደረጋል። የጡት አባት፥ የክርስትና አባት፥ እናት፥ ጓደኛ ወዘተ... አለኝታ ለማግኘት የሚደረገው ሙከራ ይህን የሚመስል ሲሆን ያለንና የታወቀን ዘመድ ጥሎ ዓይንን አብሶ፥ ጆሮን ደፍኖ ወደማይታወቅ አገር መጓዝ የተለየ ጀግንነትን ይጠይቃል!

የአባት ቤት የሚለው ቃል:- የተደላደለ፥ የተለመደ የኑሮ ሁኔታን ይጨምራል። ይህም እንዲሁ እንደ እግር አቧራ በቀላሉ አራግፎ እንደዋዛ የሚረሱት ነገር አይደለም።

እግዚአብሔር በእኛ በኢየሱስ ደም ኃጢአታችን በታጠበልንና የዘላለም ሕይወት ባገኘን ልጆቹ ሕይወት ለመሥራት፥ ከእኛ ጋር ለመሆንና ሊባርከን ሲፈልግ እንድንተው የሚጠይቀን ነገር ወይም ነገሮች ምን ይሆኑ? በስም እየጠራሁ ወንድሜ፥ እህቴ፥ ጌታ ምንድነው ተው የሚልህና የሚልሽ? ምን ይሆን ላንቺ "አገር" የሚለውን ቃል የሚተካው? "የአባት ቤት" የሚለውን ቃል የሚተካው? አሁን የምለው ለግላችን በጌታ ግልጽ ስላልተደረጉ ነገሮች አይደለም። እነዚህን በተመለከተ ግልጽ የማድረጉ ግዴታና ፋንታ የራሱ እግዚአብሔር ነው። የእኔ ጥያቄ ጌታ በግልጽ ይህን ተው (ተይ) የሚላችሁ ለእያንዳንዳችሁ ምንድ ነው? ምንድነው በእጃችሁ ጨብጣችሁ፤ በልባችሁ ቋጥራችሁ፤ በሀሳባችሁ ሞልታችሁ የታወካችሁበት ነገር? የውስጥ ቁስል:- እብጠት ፈንድቶ ደሙና መግሉ ካልወጣ በስተቀር እረፍትና ፈውስ እንደማይገኝ ሁሉ... ነፍሳችሁን ሰላም ነስቶ በረከቷንም ያገደው ነገር ምንድ ነው? ... እባካችሁ አስተንፍሱትና ተንፍሱ!!

ሁላችንም የምናውቀው የዕለት ተዕለት ልምምድ አለ፤ ይህም ልምምድ ቋሚ ሕግ ሆኗል። በዕለታዊ ኑሮአችን እንለማመደዋለን፤ በሥራ ላይ እናውቀዋለን፤ እንጠቀምበታለን። ገንዘብ ለማግኘት ገንዘብ ማውጣት ያሻል። ሎተሪ እንኳ በምኞት ሳይሆን በመግዛት ማለትም ገንዘብ በማውጣት ብቻ ነው የሚገኘው። ሎተሪ

እኒህ ወዳጇ ክብር ለጌታ ይሁንና "አሁን ሙሉ በሙሉ ተረትቻለሁ! ለተረትኩ ተረት ማረኝ!" ብለው ጌታን ይቅርታ ጠይቀዋል።■



# ምዕራፍ 3

## አብርሃምና ሣራ

ሣራ የተወለደችው አብርሃም በተወለደበት የከለዳውያን አገር በሆነችው በዑር ከተማ ነበር። ሣራ የታራ ሦስኛ ልጅ የነበረው የሃራን ልጅ ስትሆን ለአብርሃም የወንድሙ ልጅ ነች ማለት ነው። የሣራ አባት ሃራን እንደ ሌሎቹ ወንድሞቹ ረጅም ዕድሜ ሳይጠግብ ሞቷል። ታራም ዑርን ለቅቆ ወደ ከነዓን ምድር ሲሄድ አብረውት ከሄዱት ውስጥ ሣራ አንዷ ነበረች። ልክ እንደባለቤትዋ የእርሷም ስም በእግዚአብሔር ተለውጧል። ቤተሰቦችዋ ያወጡላት ስም ሦራ ሲሆን ዘለዓለማዊ አባቷ ሣራ ብሏታል። ከትርጉም አንጻር ሦራና ሣራ ብዙ ልዩነት የለውም ስለሚባል የስሙ ለውጥ ፍቺና ምክንያት ለጊዜው አልገባኝም።

ሣራ መልከ መልካም ሴት እንደነበረች ከዘፍጥረት ምዕራፍ 12 ለመረዳት ይቻላል። ስለውበቷ "አብራምም ወደ ግብፅ በገባ ጊዜ የግብፅ ሰዎች ሴቲቱን እጅግ ውብ እንደሆነች አዩ፤ የፈርዖንም አለቆች አዩአት፥ በፈርዖንም ፊት አመሰገኗት፤" ተብሎ ተመዝግቦአል።" (ዘፍ.12፥14) በውበቷ ምክንያት ወደ ፈርዖን ቤተ መንግሥት ተወስዳ የነበረ ሲሆን እግዚአብሔር ቤተ መንግሥቱን በመቅሠፍት በመምታቱ የተመለሰች ሴት ናት። ይኸው ውበቷ አቤሜሌክ የተባለውንም ባለሥልጣን የማረከ በመሆኑ አቤሜሌክ እንደወሰዳትና ከዚያም በጌታ ጣልቃ ገብነት እንደተመለሰች በዘፍ.20 ተመዝግቦአል። ሁለቱንም ጊዜ አብርሃም ሣራ "እህቴ ነች" በማለት ለተጠቀሱት ባላሥልጣኖች እንዳስተዋወቀ ተጽፏል።

ሣራ የእግዚአብሔርን ተስፋ መጠበቅ ስልችቶአት ይመስላል ባለቤቷ አብርሃም ከአገልጋይዋ ከአጋር ጋር እንዲገናኝና ልጅ እንዲወልድ ሀሳብ ያመነጨችና የመከረች ሴት ናት። ውሳኔዋ የሚያስከትለውን ውጤት በሚገባ ያላሰበችበት ይመስላል፤ ይህንንም የምክሯን ውጤት ለመቋቋም አለመቻሏ ይመሰክርባታል። አጋርን ከቤትዋ አባራ ወደ ዱር ስታሳድዳት ነፍሰ ጡርነቷ እንኳን እንድትራራ አላደረጋትምና። ባለቤትዋንም ያለ ምክንያት እንደከሰሰችው "መገፋቴ በአንተ ላይ ይሁን፤ እኔ ባሪያዬን በብብትህ ሰጠሁህ፤ እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እኔን በዓይንዋ አቃለለችኝ፤ እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካከል ይፍረድ አለችው። አብራምም ሦራን:- እነሆ ባሪያሽ በእጅሽ ናት፤ እንደወደድሽ አድርጊባት አላት። ሦራም ባሠቃየቻት ጊዜ አጋር ከፊትዋ ኮበለለች።" ከሚለው ምንባብ መረዳት ይቻላል። (ከዘፍ.16፥5–6)

ይህ የሣራና የአብርሃም ድርጊት ሌላ ትልቅ ጉዳይ አስከትሏል። ይኸውም እግዚአብሔርን ከእነርሱ ማራቁ ነው። ለስንት ዓመት መሰላችሁ? ለ13 ረጅም ዓመታት። እንዴት ሊታወቅ ይችላል? በዘፍ.16፥16 "አጋር እስማኤልን ለአብርሃም በወለደችለት ጊዜ አብራም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰው ነበረ" ተብሎ ተጽፏል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የነአብርሃምን ቤት እንደጐበኘ የተጻፈው አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በነበረ ጊዜ መሆኑን ከዘፍ.17፥1 ላይ ስለተጠቀሰ:- ከ99 ላይ 86 ሲቀነስ 13 ይቀራል። ወገኖቼ እንግዲህ ሕይወታችንን እንመርምር በድርጊታችን፥ በጥፋታችን ጌታን ከሕይወታችን ከቤታችን ከአገልግሎታችን እንዳናርቅ እንጠንቀቅ ዘንድ የአብርሃም ሕይወት ያስተምረናል።

ከዚህ የሣራ ምክርና ከተከታዮቹ ሁኔታዎች፥ ለዛሬው የትዳር ሕይወታችን ብዙ ቁም ነገር ማትረፍና መሸመት ይቻላል። ጌታ የዘገየ ሲመስላችሁ ባልና ሚስቶች ምንድነው የምታደርጉት? አቋራጭና አማራጭ ዘዴ መሻት? ወይስ እንደ ዕንባቆም



"በመጠባበቂያዬ ላይ እቆማለሁ፥ በአምባ ላይም እወጣለሁ፤ የሚናገረኝንም፥ ስለክርክሬም የምመልሰውን አውቅ ዘንድ እመለከታለሁ" እንላለን? (ዕንባቆም 2፥1) ነገሮች በቤት ውስጥ ሲሻክሩ ባል ሆይ ለሚስት ምን ምክር ትሰጣለህ? መፋታት እኮ ይቻላል በእኛ አልተጀመረም... ወዘተ እንል ይሆን? ነገር ግን ሳናመዛዝን የምንናገረው ነገር ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። ሳንጸልይበትና በረጋ አእምሮ ሳንሆን የምንዘረግፈው ቁጣም ሆነ ምክር ትዳርን ያተራምሳል። የዘመናት ፍቅርን ያስረሳል። እሳተ ገሞራ ሲፈነዳ አካባቢውን እንዳልነበረ እንደሚያደርግ ያሉትን ጣፋጭ ትውስታዎች፤ ትላልቅ ውለታዎችና የፍቅር ገድሎች ላይ ረመጥ የድንጋይና የአፈር ክምር ያለብሳል። ወገኖቼ፥ ባሎች፥ ሚስቶች:- ንግግራችሁ፥ አስተያየታችሁ የሚያስከትለውን ውጤት ሳትመረምሩና መንፈስ ቅዱስን ሳታስመረምሩ አትዘርግፉት! ለዚህም ጌታ ይርዳን። ይገርማችኋል አንዳንድ ነገሮችን አለመናገር ምንኛ ይሻላል? ትላንት ዛሬ ቢሆን የተሻልሁ ባል ሳልሆን አልቀርም ብላችሁ እንዳትፀፀቱ መጠንቀቁ መልካም ነው። እኔ ይህንን አባባል አልፌበታለሁ።

ሣራ ዕድሜዋ ካለፈና የሴት ወግ ከተለያት በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት የተስፋውን ልጅ ይስሐቅን ወልዳ 37 ዓመታት ከኖረች በኋላ በ127 ዓመት ዕድሜ በቂርያትአርባቅም ሞተች። አብርሃምም አልቅሶ "...ኬብሮን በምትባል በመምሬ ፊት በከነዓን ምድር ባለው እርሻ ባለ ድርብ ክፍል በሆነው ዋሻ ውስጥ ቀበራት።" (ዘፍ.23፥19–20)

የጌታ ሰዎች ለአዲስ ተጋቢዎች ምርቃት ሲሰጡ "የአብርሃምና የሣራ ጋብቻ ይሁንላችሁ!" የሚሉት ለምን ይሆን የሚል ጥያቄ አዘውትሮ በአእምሮዬ ይመላለሳል። ምናልባትም አንዱ ምክንያት ለባልዋ ካላት አክብሮት ሊሆን ይችላል። ሣራ አብርሃምን "ጌታዬ" ብላ መጥራቷ (ዘፍ.18፥12) ፍጹም ታዛዥ

ለእኔም ለመሰሎቼም አእምሮ በጎ የሆነ ሁሉ ያማረ፣ የተስተካከለ ነው። መታመም በጎ ነው ብሎ መውሰድ ያስቸግራል። በልዩ ልዩ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ በጎ ነው ማለት አእምሯችን የለመደውን–ልሙጥ ልማድ ይቃረናል። እግዚአብሔርና አንዳንድ የእርሱ ነገር የገባቸው ሰዎች "በጎ" የሚለውን ቃል የሚረዱት ለየት ባለ ሁኔታ እንደሆነ ትንሽ የገባኝ ይመስለኛል።

ዳዊት በዝማሬው "እግዚአብሔር በለመለመ መስክ ውስጥ ያሳድረኛል" ይላል። (መዝ.23) የዳዊትን ሕይወት ሳይ ግን ብዙ ጊዜ በደረቅ ምድር፣ በዱር በበረሐ አድሯል። የገባው ገብቶት ቅኔውን ስለተቀኘ የሚለውን እቀበላለሁ። ስንቶቻችን የአምላክን ፈቃድ በትዕግሥትና በእምነት እንቀበላለን?

በኢየሩሳሌም በበጎች በር አጠገብ ቤተሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች። በዚችም መጠመቂያ አጠገብ የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞች፣ ዕውሮች፣ አንካሶች፣ ሰውነታቸው የሰለለ ብዙ ሰዎች ይተኙ ነበር። የዚህን መጠመቂያ ውኃ መልአክ መጥቶ ሲያንሳቅሰው መጀመሪያ የገባ ማንም ሰው ከያዘው ከማናቸውም ዓይነት ደዌ ይፈወስ ነበር። (ዮሐ.5፥2–4) ታሪኩን እናተኩርበት።

አንድ ከምንም ዓይነት ደዌ ፈውስ ሊሰጥ የሚችል መጠመቂያ አለ። የሚፈውሰው ግን ውኃው ሲነቃነቅ ብቻ ነው። ውኃውን የሚያነቃንቀው ከመጠመቂያ ውጭና በላይ የሆነ ኃይል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸው ሰዎች በዚያ በመጠመቂያው አካባቢ አሉ እየተጠባበቁ። ከእነሱም እያንዳንዱ ሊፈወስ ይፈልጋል። ለመፈወስ ግን ውኃው መንቀሳቀስ አለበት። ከደዌ ለመፈወስ ልክ በወኃው እንቅስቃሴ ጊዜ ከማንም ቀድሞ ወደውኃው መግባት ያሻል። ውኃው ለወር ከዚያም አልፎ እስከ ዓመትም ላይንቀሳቀስ ይችላል። የታመሙት በችግር ላይ ያሉት የውኃውን መንቀሳቀስ ይናፍቃሉ፣ ይመኛሉ፣ ይጓጓሉ። መቼ ይህ ውኃ



ተንቀሳቅሶ ዕውርነቴ በርቶ፣ አንካሳነቴ ቀርቶ፣ እንደሰው ዘልዬ፣ መቼ ከዚህ ደዌ ተፈውሼ በማለት በዚያ ሥፍራ የተሰበሰቡ ድውያንና ችግረኞች አንዱ ለሌላው የራሱን በሚያሳዝን ሁኔታ ሲተርክ ይታየኛል። መቼ ይሆን የሚል የጣርና የሲቃ ድምፅ እያሰሙ:- ዛሬም መጠበቅ፣ ነገም መጠበቅ። መቼ ይሆን የእግዚአብሔር ክንድ የሚንቀሳቀሰው? ጸሎቴን ሰምቶ የሚመልሰው? እናንተ ዛሬ በመጠመቂያ ሳይሆን በጌታ እግር ሥር የምትገኙ የጌታ ልጆች ይህ ጥያቄአችሁ ሊሆን ይችላል፤ ተንቀሳቀስ አንተ ውኃ፣ ምነው ተንቀሳቅሰህ እንደማታውቅ ሆንህ፣ መንቀሳቀሱን ረሳኸው፣ ችግሬ በዛብኝ፣ ...ጨረሰኝ፣ ቁመቱም ረዘመ፣ ልቋቋመው አልቻልኩም። የናስ ቁር አለው፣ ጥሩር ለብሷል፣ ባለገምባሌ ነው፣ ትከሻው በጥሩር ተሸፍኗል፣ ጦሩ ከባድ ነው፣ ላሸንፈው አልችልም፣ ወደታች ያየኛል፣ እኔ ወደ ላይ አየዋለሁ...!።

መቼ ነው የምትንቀሳቀሰው? ፍርሐቴንና ድንጋጤዬን፣ ሐፍረቴንና ጉስቁልናዬን የምትገፍፈው? በዚህ ሁኔታ ላለህ ወገኔ ጭቃ መርገጡ፣ ጡብ መሥራቱ፣ መሸከሙ፣ ከጅራፍ ጋር ሲሆን ይመራል። ያንገሸግሻል። ይስሐቅን መጠበቁ አቤት ሲያሰለች! መቼ ነው የይስሐቅ መምጣት? (የጌታ ተስፋ መፈጸም) መቸ ነው ከችግሬ የምገላገለው? መጠመቂያው (ጌታ አምላክ) የሚንቀሳቀሰው መቼ ነው? ዓመታቱ ተሰለፉ ይኼው ፊቴ ተጨማደደ፤ እድሜ ከድቶኛልና። ሽበት ሲያደራብኝ ሰውነቴ ሲጨመቅ ቀኖቼ ሲጨለጡ እያየህ... መቼ ነው የምትንቀሳቀሰውና ከዚህ ችግር የምላቀቀው? "እንኳን ሊያፀድቁኝ በቅጡ በኮነኑኝ" መንገሱን ተወው አይታለምም አይታሰብም። ሳሙኤል እራሴን ሲቀባኝ በግንባሬ ወርዶ መሬት እንደተንጠፈጠፈው ዘይት ያለፈ የቀረ ነገር ነው። በእኔና መሞት መካከል አንድ እርምጃ ያህል ቀርቷል። (1ሳሙ.20፥3) አሁንማ "መንገሤን ሳይሆን የምጠባበቀው የሳዖል ሰይፍ መቼ ይበላኛል ጦሩ መቼ ይወጋኛል" ብዬ ነው። ተስፋዬ ወደ ሥጋት ተለውጧልና።

እስከ መቼ ነው? ከሚሉት መካከል ሁልጊዜ ናፍቆቱና ምኞቱ ኢየሱስን መምሰልና የኢየሱስን ትንሣኤ ማወቅ የነበረው ሐዋርያው ጳውሎስ ይገኛል። ከባድ ሥጋዊ ሕመም ነበረበት። የሥጋ መውጊያ፣ ጎሳሚ ነበረው።

ያም እንዲወገድለት እየጸለየ ሲጠብቅ መቼ ይወገድልኛል? ሲል ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፤ ሁለተኛ ጸለየ፤ ምንም ለውጥ አልመጣም፤ ሦስተኛ ጸለየ መልሱ መጣ። መልሱ ግን ከነበረበት ሁኔታ መፈወስ መላቀቅ አልነበረም። በሚጠብቀው መፍትሔ ፈንታ እግዚአብሔር "ፀጋዬ ይበቃሃል፣ ኃይሌ በድካም ይፈፀማልና" (2ኛቆሮ.12፥7–9) ሲል ተናገረው። ከልመናው አንፃር ሲታይ ለጥያቄው በጠያቂው ፍላጎት መሠረት አልተመለሰም።

የሙሴንና የጳውሎስን ምሳሌ ስለምን ጠቀስሁ? እናንተ "መቼ ነው" ባዮች ልብ አድርጉ ልብ እናድርግ። የዕጣ ድርሻችሁ የሙሴ ሊሆን ይችላል። ያማራችሁን እንደአሰባችሁት ላትታቀፉትና ላትኖሩበት ትችላላችሁ። ከችግራችሁ ጋር እየኖራችሁ በጌታ መጽናናታችሁ ለእናንተ የጌታ ፈቃድ ሊሆን ይችላል። በሙሴ ላይ ለምን ይህ ሆነ? ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ከአብረሐም ያነሰ ተወዳጅነትና ተቀባይነት ስለነበረው ይመስላችኋል? አይደለም። እግዚአብሔር ሙሴን እጅግ ይወደው ነበር፣ እጅግ ይኮራበት ነበር። "እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ...በእስራኤል ዘንድ አልተነሳም..." (ዘዳ.34፥10) የእግዚአብሔር ምስጢረኛ። ጳውሎስም "በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና" (ሐዋ.ሥራ 9፥15) ተብሎ በአምላክ የተመሰከረለት ታላቅ ሰው ነበር።

ወገኔ ሆይ የውኃውን መንቀሳቀስ ጠብቅ። ለዚህም በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ፀጋ በርታ። ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጥህ። አሜን።■





ሆኜ ስታይና በእርሱ አማካይነት ስቀርብ "እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ የለብኝም። በንጹህ በኢየሱስ ንጹህ ሆኛለሁ።" ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

የባርነት ቀንበሮች ሁሉ ዋነኛ የሆነው የኃጢአት ባርነት ቀንበር ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባደረገው ቤዛነት ተሰብሯል!! ስለዚህም አሁን ኃጢአትን ረግጠን ከሳሻችንን ዲያብሎስን አሳፍረን ቀና ብለን መሄድ እንችላለን። ለኔ "የባርነታችሁን ቀንበር ሰብሬአለሁ ቀና ብላችሁ እንድትሄዱ አድርጌአችኋለሁ" የሚለው ቃል ወደ ክርስቶስ መስቀል ያመለክተናል። መስቀሉ የኃጢአትን ቀንበር ሰብሮልናል። ስለዚህም ቀና ብለን እንሄዳለን። አዲሲቷን ኢየሩሳሌም እንወርሳለን። ለወደደንና በደሙ ላጠበን ለበጉ ክብር ይሁን አሜን።

አሁን ወደተነሣንበት አብይ ነጥብ እንመለስ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደስታና ሐዘንን ጎን ለጎን በማቅረብ ትዝ ከሚሉኝ ምዕራፎች ውስጥ ዘፍጥረት 21 እና 22 ይገኛሉ። በዘፍ.21 እግዚአብሔር እናታችንን ሣራን እንደጐበኘ፥ የአብርሃምና የሣራን ቤት ሙሉ በሙሉ በደስታ እንደሞላ እናያለን። እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ የእነርሱ የሆኑት ሁሉ የዚህ ደስታ ተካፋዮች ነበሩ። የዚያን ዕለት ፀሐይ፥ ሰማይም ሆነ መሬት ልዩ ጣፋጭ ድምፅ የተሞላ ዜማ ሳያሰሙ የቀሩ አይመስለኝም። "እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎልኛልና" አለች ሣራ። በአንጻሩ ደግሞ ከቤታቸው ሳቅ ጥርግርግ ብሎ እንደወጣ በብርሃን ፋንታ ጨለማ፥ በሳቅ ፋንታ ሐዘን ገብቶ ተንሰራፍቶ እንደነበረ በዘፍጥረት 22 ተመዝግቦ እናገኛለን።



በዚህም የተነሣ የአብርሃም ሕይወት ቋንቋ ሊገልጠው ከሚችል በላይ በሆነ ችግርና ፈተና ውስጥ ሲያልፍ እናየዋለን። እንደ ማዕበል የሚያዋልል ሐሳብ በዚህ በደስተኛ ቤት ገባ። የበጋ ወይም የኋላ እሸት የሆነው አንድያ ልጃቸው ይስሐቅ በእግዚአብሔር ተፈለገ። ለጊዜው አይደለም፥ እንደ ሳሙኤል ለአገልግሎት አይደለም! ለመስዋዕትነት ያውም ለሞት! "...እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው! እንዲህም አለው:- አብርሃም ሆይ "የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ! እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ (ይስሐቅን) መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው።" (ዘፍ.22፥1–2)

ትዕዛዙ ቀጥተኛና ግልፅ ነው። ተጨማሪ መመሪያ ወይም ማብራሪያ የሚያሻ አይመስልም። የትእዛዙ ምንጭም የታወቀ ነው። ከእንግዳና ከማይታወቅ ምንጭ አልመጣም። አዛዡ "ከአገርህ፥ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ! ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ..." ያለው አምላክ ነው። አዛዡ "አብራም ሆይ አትፍራ፥ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው" ያለ ጌታ ነው። አዛዡ "የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነቱ እመለሳለሁ! ሚስትህም ሣራ ልጅን ታገኛለች" ያለው ነው። ድምፁም ያው ነው። የንግግሩ ይዘት ግን ተለውጧል። ዜናው የአብርሃምን አእምሮ የሚበጠብጥ ልቡን የሚያናውጥ ነበር። በእርግጥም ይግባኝ የሚያሰኝ ወይም የሚያስጠይቅ ነው። በቃል ኪዳን የመጣ፥ ሊተካ የማይቻል ለቤተሰቡ የመኖር ትርጉም የሰጠው የዓይን ሁሉ መስህብ፥ ብቸኛ የሆነው ወራሽ ከወላጆቹ ማለትም ከአውራሾቹ ቀድሞ እንዲሞት ተጠየቀ! ግን በእግዚአብሔር ላይ ይግባኝ ተብሎ ወደ ማን አቤት ይባላል!?

በዚያን ሌሊት አብርሃም ሲወራጭና ሲገላበጥ ሳያድር አልቀረም፤ ያውም ምናልባት መደብ ወይም አልጋ ላይ መውጣት ከቻለ ማለት ነው። ለሚስት

የተቸገረ ሰው የማይሆነው ነገር የለም፣ "የጨነቀው እርጉዝ ያገባል" ይላሉ አበው። "የቸገረው በቅቤ ይበላልም" ይባላል አማራጭ የማጣትን አጋጣሚ ለመግለጽ። እነዚህ ሕይወትና የረጅም ጊዜ ልምድ የወለዳቸው አባባሎች ሰፊ ጥልቅ ትርጉም አላቸው።

ፈተና ለረጅም ጊዜ የማይለይ የቅርብ ጓደኛ ከሆነላቸውና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች አንዱ ዳዊት ነው። ችግርና ፈተና ጤናማን እንደ እብድ፥ አዋቂን እንደ ሞኝ ያደርጋሉ። ጉብዙንም ጀግናውንም ፈሪና ሰነፍ ያደርጉታል፥ ያኮራምቱታል። ከዚህ አንጻር ዳዊት የሆነውንና በ1ኛሳሙ.21፥10–15 የተመዘገበውን እንመልከት።

"ዳዊትም ተነሣ በዚያም ቀን ሳኦልን ፈርቶ ሸሸ፥ ወደ ጌትም ንጉሥ ወደ አንኩስ ሄደ። የአንኩስ ባሪያዎችም:- ይህ ዳዊት የአገሩ ንጉሥ አይደለምን? ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም እልፍ ገደለ ብለው ሴቶች በዘፈን የዘመሩለት እርሱ አይደለምን? አሉት። ዳዊትም ይህን ቃል በልቡ አኖረ፥ የጌታንም ንጉሥ አንኩስን ፈራ። በፊታቸውም አእምሮውን ለወጠ፥ በያዙትም ጊዜ እንደ እብድ ሆነ፤ በበሩም መድረክ ላይ ተንፈራፈረ፥ ልጋጉም በጢሙ ላይ ይወርድ ነበር። አንኩስም ባሪያዎቹን:- እነሆ፥ ይህ ሰው እብድ እንደሆነ አይታችኋል፤ ለምን ወደ እኔ አመጣችሁት? በፊቴ ያብድ ዘንድ ይህን ያመጣችሁት እብድ ጠፍቶብኝ ነውን? እንዲህ ያለውስ ወደ ቤቴ ይገባልን? አላቸው።"

የዳዊትን ችግር እንረዳለት። ከሳኦል በዝናው ምክንያት ሲሸሽ ዝናው ከንጉሥ አንኩስ ጋርም የሚያጋጨው መሰለው። ስለዚህ ዘዴ መሻቱ ነው። ወገኖቼ:- አንዳንድ ፈተናዎች አደባባይ ላይ ባያንፈራፍሩንም ውስጣችንን አላንፈራፈሩንም? ምን ይሆን ይህ ልጋግ እስከማውጣት "በወግ በማዕረግ



በውስጣችን ያለውን" አውጥተን በሥራና በጥቅም ላይ እንዳናደርግ የሚያስገድደን? የውበቱን ነገር ወደ አስጸያፊነት የሚወስድብን ወይም ልውሰድ እያለ የሚሟገተን ፈተና? ልብ አድርጉ ይህ የዳዊት ፈተናም አልፏል። ዳዊትም እግዚአብሔር እንዳለ በእግዚአብሔር ጊዜ ነግሷል። ጌታ ለእያንዳንዳችሁም እንዲሁ የገባውን ተስፋ ይፈጽማል፥ ጠብቁት።

የኤርምያስንም ሕይወት ጠለቅ ብለን ስናይ ፈተና እጅግ ያንገላታው፥ ያለ ልጓምና ገደብ የተለቀቀበት ይመስላል። ስለዚህም ኤር.20፥14–18:- "የተወለድሁበት ቀን የተረገመች ትሁን፤ እናቴ እኔን የወለደችባት ቀን የተባረከች አትሁን። ወንድ ልጅ ተወልዶልሃል ብሎ ለአባቴ የምሥራች ነገር ደስ ያሰኘው ሰው የተረገመ ይሁን። ያም ሰው እግዚአብሔር ሳይጸጸት እንደገለበጣቸው ከተሞች ይሁን፥ በማለዳ ልቅሶን በቀትርም ጩኸትን ይስማ፤ እናቴ መቃብር ትሆነኝ ዘንድ ማኅፀንዋም ዘወትር ይዞኝ ያቆይ ዘንድ በማኅፀን ውስጥ አልገደለኝምና። ድካምንና ጣርን አይ ዘንድ ዘመኔም በእፍረት ታልቅ ዘንድ ስለ ምን ከማኅፀን ወጣሁ?" ሲል ይሰማል።

የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከፈተና ውጭ አልነበረም። ስለዚህም የጌታ ቃል:- "እንግዲህ በሰማያት ያለ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ፀንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ። ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም"። (ዕብ.4፥14–15) በማለት ስለ ጌታ ኢየሱስ ይመሰክራል። ጌታ ኢየሱስ የምድር ዘመኑ የተደመደመው በእሾህ አክሊል ነበር። በአባቱ ዘንድ ግን የባለ ብዙ አክሊሎች ጌታ ሆነ።

ወገኖች የጥንቶቹንና የዛሬዎቹን የእግዚአብሔር ጀግኖችንና አርበኞችን የጓዳና ጥልቅ የጭንቀት ሕይወት በውስጣቸው የተፈራረቀውን ፈተናና ችግር እንደዚሁም

እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ሚስቱንም ባሪያዎቹንም ፈወሳቸው፥ እነርሱም ወለዱ።" (ዘፍ.20፥17)

ከአብርሃም ብዙ ጸሎቶች፥ በዘፍ.18፥22–33 ባለው ብቻ እናተኩር። "ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ፥ ወደ ሰዶምም ሄዱ፤ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር። አብርሃምም ቀረበ አለም:- በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን? አምሳ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? ከተማይቱንስ በእርሷ ስለሚገኙ አምሳ ጻድቃን አትምርምን? ይህ ከአንተ ይራቅ፤ ጻድቁን ከኃጢአተኛው ጋር ትገድል ዘንድ፥ ጻድቁም እንደ ኃጢአተኛው ይሆን ዘንድ፥ እንደዚህ ያለ አድራጎት ከአንተ ይራቅ። የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን? እግዚአብሔርም:- በሰዶም በከተማይቱ ውስጥ አምሳ ጻድቃን ባገኝ ሥፍራውን ሁሉ ስለእነርሱ እምራለሁ አለ። አብርሃምም መለሰ አለም እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ እነሆኝ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፤ ከአምሳው ጻድቃን አምስት ቢጎድሉ ከተማይቱን ሁሉ በአምስቱ ምክንያት ታጠፋለህን? ከዚያ አርባ አምስት ባገኝ አላጠፋትም አለ። ደግሞም ተናገረው፥ እንዲህም አለ:- ምናልባት ከዚያ አርባ ቢገኙሳ? እርሱም:- ለአርባው ስል አላደርገውም አለ። እርሱም ጌታዬ አይቆጣ እኔም እናገራለሁ ምናልባት ከዚያ ሠላሳ ቢገኙሳ? አለ። እርሱም ከዚያ ሠላሳ ባገኝ አላጠፋም አለ። ደግሞም እነሆ፥ ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፤ ምናልባት ከዚያ ሃያ ቢገኙሳ? አለ። እርሱም ከዚያ ሃያ ቢገኙ ስለ ሃያው አላደርገውም አለ። እርሱም እኔ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ብናገር ጌታዬ አይቆጣ፤ ምናልባት ከዚያ አሥር ቢገኙሳ? አለ። እርሱም? ስለ አሥሩ አላጠፋትም አለ። እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ሥፍራው ተመለሰ።"



አብርሃምም ሲጸልይ ወደ እግዚአብሔር የቀረበው በታላቅ አክብሮት ነው። "አብርሃምም መለሰ አለም:- እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ እነሆ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፤" ቁ.27። አብርሃም የእግዚአብሔርን ማንነት ያውቃል፥ የራሱንም ማንነት ያውቃል። ብዙዎቻችን ይህ በጣም ግልጽ የሆነልን አይመስለኝም። ራሳችንን ጻድቃን አድርገን እንወስዳለን። ምናልባት ከአካባቢያችንና ከምናውቃቸው አንዳንድ ክርስቲያኖችም ጋር ራሳችንን በማነጻጸር እንዲህ ዓይነት ስሜት ሊመጣብን ይችላል። እንደ ፈሪሳዊው ጸሎተኛ የምናደርገውን ምጽዋትና የምንከፍለውን አሥራት እንቆጥር ይሆናል። ለጸሎት የምንንበረከክበትን ጊዜ፥ ቃሉን ለማንበብና ለማስተማር የምናሳልፈውን ጊዜ እናስብ ይሆናል። ከእህልና ከውኃ ለጸሎት የምንወገድበትን ጊዜ እናስብ ይሆናል። እነዚህ ሁሉና ሌሎችም "መልካም ሥራዎቻችን" ከሌሎቹ ክርስቲያኖችና ከአካባቢያችን የተሻልን ሊያስመስሉን ይችላሉ። ዞር ዞር ግን፥ ወገኔ ሆይ ያንተ ጽድቅ በጌታ ፊት የመርገም ጨርቅ ነው። ከቁጥር አይገባም። ሁላችን በእግዚአብሔር ፊት አመድና አፈር ነን።

ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በማየቱ ደንግጧል፤ የእግዚአብሔር ክብርና ጽድቅ አእምሮው ካሰበው በላይ ስለነበር። "እኔም" ይላል ኢሳይያስ፤ "ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊት ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለአዩ ጠፍቻለሁ ወዮልኝ አለ።" አብርሃምም የራሱን ደካማነት፥ በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በሚገባ የተረዳ ሰው ነበር።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ከተመዘገበው የአብርሃም ጸሎት የምንረዳው ሌላው ነጥብ በጀመረው ነገር ሳይሰለች የሚገፋበት መሆኑን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ድርድር ጀመረ፤ 50 ከዚያ 45፥ ከዚያ 40 እያለ እስከ 10 ሲወርድ

ግድ በለው። እግረ መንገዴን እግዚአብሔርን በምን እያወከኸው ነው ያለኸው ብዬ ልጠይቅህ? እግዚአብሔርን በምን ይሆን ዕረፍት እየነሳህ ያለኸው? ሕይወትህ ለጌታ እንደ ሰዶምና ገሞራ ከተማ ሆኖበት ይሆን? እባክህ ጌታን አታሳዝነው።

አንዳንድ ሰዎች አብርሃም ለምን በ10 ጻድቃን ላይ አቆመ? ለምን 5 ወይም 2 ጻድቃን ቢገኙ ማርልኝ አላለም በማለት ይጠይቃሉ። ለዚህ ጥያቄ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ሲመልሱ አብርሃም የጸለየው እግዚአብሔር ያደርጋል ብሎ የሚያምነውን ያህል ብቻ ነበር። የአብርሃም ግምትና በዚያን ጊዜ የነበረው እምነት ከ10 ጻድቃን በታች ለመጠየቅ የሚያስችለው አልነበረም። አብርሃም እግዚአብሔር ያደርጋል ብሎ ከሚያምነው በላይ አልጠየቀም ብለዋል። ከዚህ መልስም ስለ ራሳችን ጸሎት የምንማረው አለን። ለመሆኑ አንድን ነገር ጌታን ስንጠይቅ በእርግጥ ያደርገዋል ሊያደርገውም ይችላል የምንለውን ያህል ነው? ለመሆኑ አንድን ነገር ስንጸልይ፥ ስንጠይቅ የምራችንን ከአንጀታችን ነው? አብርሃም የሚጠይቀውን ለመቀበል እምነትና የልብ ዝግጅትም ነበረው። ሰዶምና ገሞራ ኚደደች። ምናልባት የነበሩት ጻድቃን ከ10 በታች ሆነው ይሆናል። ሆኖም ግን በአብርሃም ጸሎት ሎጥ መዳኑን "እግዚአብሔርም እነዚያን የአገር ከተሞች ባጠፋ ጊዜ አብርሃም አሰበው፤ ሎጥ ተቀምጦበት የነበረውንም ከተማ ባጠፋ ጊዜ ከዚያ ጥፋት መካከል ሎጥን አወጣው።" ተብሎ የተጻፈው ቃል ያስረዳል። (ዘፍ.19፥29)

ለመሆኑ እኛ ስንጸልይ የምራችንን፥ ጌታን በማመንና በመጠበቅ ነው ወይ? ለመሆኑ የጸሎታችን ውጤት ሊያስከትል የሚችለውን መልስ በሚገባ አስበን ለመቀበል ዝግጁ ነን? እግዚአብሔር ሆይ በሕመሜም፥ በጤንነቴም፥ በማግኘቴም፥ በማጣቴም፥ በክብሬም፥ በውርደቴም ላመስግንህ፣ ላክብርህ፣ እንላለን? ጌታ ሆይ መሣሪያህ አድርገኝ፥ ተጠቀምብኝ እንላለን? ግን ለዚህ



ላመቻቻችሁ (ላዘጋጃችሁ) ቢለን ኡ.ኡ እንላለን። ይህን ሳስብ አንድ ምሳሌ በአእምሮዬ ስለመጣ ላካፍላችሁ። "አንድ ሰው ነበር። እርሱም አንድ ጥሩ ሰጋር በቅሎና ጉልበተኛና ጋላቢ ፈረስ ነበረው። ይህ ሰው ከሚጋልብ ፈረስ ይበልጥ የሚሰግር በቅሎን ወይም ፈረስን ይወድ ስለነበረ ብዙ ጊዜ የሚቀመጠው በበቅሎ ላይ ነበር። ታዲያ ይህ ፈረስ "ጌታዬ በደንብ ይቀልበኛል፥ በደንብ ይይዘኛል ግን በበቅሎው እንደሚጠቀም በእኔ አይጠቀምም፤ ምነው እንደ በቅሎው በእኔም በተጠቀመ?" ብሎ አሰበ። "ምናልባትም አይወደኝ ይሆናል። የበለጠ የሚወደው በቅሎውን ነው፤ ግን እስቲ ልጠይቀው" አለና ጌታው ቢጠቀምበት እጅግ ደስ እንደሚለውና ሙሉ ፈቃደኛ እንደሆነ ገለጸለት። በፈለገው መንገድ ሊጠቀምበት እንደሚችልም ለጌታው ነገረው። የፈረሱ ጌታ ፈረሱን ለመጠቀም የፈለገው ከጋላቢነት ወደ ሰጋርነት በመለወጥ ነው። ስለዚህም ፈረሱን ራሱን ሊያገለግለው በሚችል መንገድ ማሠልጠን ጀመረ። ለዚህም በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ፈረሱ ጋላቢነቱን ማለትም የድሮ ልምዱን ይረሳ ወይም ይተው ዘንድ ሁለት እግሮቹን መሰንከል ነበር። መታሰሩ ለፈረሱ ግራ ገባው። ነፃነቱን ነሣው። እንደ ልብ መሮጡን መተው ነበረበት። ከዚህም በላይ እስራቱ እግሮቹን አሳመሙት። በፊት ያምሩ በነበሩት እግሮቹም ላይ አሁን ገመዱ ያረፈበት ጠባሳ ወይም ምልክት በማኖሩ የሚኮራበት ውበቱ ቀነሰ። የፈረሱ ጌታ ሌላ የወሰደው እርምጃ ለፈረሱ መስገር ማስተማር ነበር። ይህም ቶሎ አልገባው ስላለ ለረጅም ጊዜ በአለንጋ መገረፍ ነበረበት። ከብዙ ጊዜ መታሰር፥ ከብዙ ጊዜ የችግሮቹ መቁሰል፥ ከብዙ ጊዜ አለንጋ በኋላ ደንገላሣ ግልቢያው በመስገር ተተካ። በሁኔታው ረካ። በዚያን ጊዜ የፈረሱ እግሮች ተፈቱ፥ አለንጋው ቀረ። ጌታውም ፈረሱ በፈለገው ዓይነት አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን አየ፤ ሊጠቀምበትም ጀመረ። እስከዚህ ድረስ ግን ፈረሱ እጅግ አዘነ። ሁኔታውም ያልገባው ስለነበረ ግራ ተጋባ። ለማገልገል በመፈለጉ መታሰሩ፥ መቁሰሉ አጉል ኪሣራ የደረሰበት መሰለው።

የአንዳንዶቻችንም ሁኔታ ከፈረሱ ሁኔታ ብዙ አይለይም፤ ነገሩን የምንረዳው ጫፉን ስናይ ብቻ ነው።■



## መደምደሚያ

ንጉሡ አርጤክስስ አንድ ጊዜ በሥልጣን ከሱ ቀጥሎ ያለውን ሐማ የተባለውን ሰው አንድ ጥያቄ ጠየቀው። ጥያቄውም እንደዚህ የሚል ነበር። "ንጉሡ ያከብረው ዘንድ ለሚወድደው ሰው ምን ይደረግለታል?" ሐማም ለዚህ ጥያቄ እንደዚህ ሲል መለሰ:- "ንጉሡ ያከብረው ዘንድ ለሚወድደው ሰው እንዲህ ይደረግ፤ ንጉሡ የለበሰው የክብር ልብስ፥ ንጉሡም የተቀመጠበት ፈረስ ይምጣለት፥ የንጉሡም ዘውድ በራሱ ላይ ይደረግ፤ ልብሱንና ፈረሱንም ከንጉሡ አዛውንት በዋነኛው እጅ ያስረክቡት፤ ንጉሡም ያከብረው ዘንድ የሚወድደውን ሰው ያልብሱት፤ በፈረሱም ላይ አስቀምጠውት በከተማይቱ አደባባይ ያሳልፉት፤ በፊቱም:- ንጉሡ ያከብረው የሚወድደው ሰው እንዲህ ይደረግለታል ተብሎ አዋጅ ይነገር።" አለ። ንጉሡም ይህንኑ ያልከውን ለመርደክዮስ አድርገው አለው።

የአብርሃምንና የእግዚአብሔርን ግንኙነት የሚመለከተውን ይህን መጽሐፍ ለማጠቃለል ይህን የአርጤክስስንና የሐማን ውይይት መሠረት ማድረግ ይቻላል። አብርሃም በታላቁ ንጉሥ በእግዚአብሔር በጣም የተወደደ ሰው ነበር። ለዚህም ማስረጃው እግዚአብሔር ራሱን ለአብርሃም እሱነቱን ለአብርሃም ጥቅምና ፈቃድ ሲሰጥ ማየት ነው። ይህን የሚገልጽልን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዘፍ.22 ነው።

በዘፍጥረት 22፥16 ላይ "እግዚአብሔር እንዲህ አለ በራሴ ማልሁ ይህን ነገር አድርገሃልና፥ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤ የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ። ቃሌን ሰምተሃልና።" የሚል ተመዝግቦ እናገኛለን። በዚህም እግዚአብሔር በሁሉም አንፃር

ለአብርሃም ሲገኝ ይታያል እግዚአብሔር በዚህ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ ወደ አብርሃም ከመቅረቡ በፊት ግን አብርሃም በራሱ ላይ ተጭነውት የነበሩትን ነገሮች ደረጃ በደረጃ እንዲያወልቅ የተደረገ መሆኑን መረዳት ትልቅ መንፈሳዊ ግንዛቤና መረዳት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ልዩ ልዩ ምዕራፎች እንዳየነው አብርሃም አገሩን፥ ዘመዶቹንና የአባቱን ቤት እንዲተው ተደርጓል። ቀጥሎም ለብዙ ዓመታት ያህል አጫዋቹና የዓይኑ አምሮት የነበረው እስማኤል ከእናቱ ከአጋር ጋር ከአብርሃም እንዲለይ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የተስፋ ልጅ የሆነው የአብርሃምን የወደፊት ዘር ያስጠራል፥ ያስቆጥራል፥ እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሰጠውን ሃብትና ንብረት ይወርሳል ተብሎ የተጠቀሰውና በእግዚአብሔር በራሱ የተሰየመው ይስሐቅ በምዕራፍ 22 ላይ በመሠዋት እንዲሰጥ ወይም ለመሥዋዕት እንዲቀርብ ሆኗል። በአብርሃም በኩል ሆነን ስናየው ይስሐቅ እኮ ተሠውቷል።

አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔርን በሚመችና በሚያስደስት መልክ ይጣበቅ ዘንድ የመጨረሻ አለኝታ የሆነው የተስፋው ልጅ ለመሥዋዕት መቅረብ ነበረበት። የዚህ መጽሐፍ ዋናው መልዕክት ይህ ነው። አብርሃም ወዳጄ ተብሎ በእግዚአብሔር እንዲጠራ አብርሃም ከብዙ ነገሮች መለየት ነበረበት። አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ እግዚአብሔርም በአብርሃም ላይ እንዲጣበቅ አብርሃም ያከማቻቸውና አለኝታ ያረጋቸው አያሌና ልዩ ልዩ ነገሮች በየደረጃውና በየወቅቱ እየተገፈፉ መወገድና ለእግዚአብሔር ሥፍራ መስጠት ነበረባቸው።■



ወገኖች ሆይ!

በቀናተኛነቱ የማያፍረው አምላካችን የእናንተ ይሆን ዘንድ በእያንዳንዳችንና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ነገር ሁሉ እንዲወገድ ይህንንም እግዚአብሔር እንዲያደርገው መፍቀድ ይኖርብናል። በሌላ አነጋገር አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ለመጣበቅ ይበቃ ዘንድ የዛፍ ግንድ እንጨቱ እስኪገኝ ድረስ በላዩ ላይ ያለው ልጥ እንደሚላጥ ሁሉ እንደዚሁ ከአብርሃም ላይ ብዙ ነገሮች መወገድ ነበረባቸው። በዚያም የአብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅነት ምስጢር ትርጉም ያገኛል ማለት ነው። እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት በልባችን ውስጥ ያጉላልን።

ይህን መጽሐፍ የምታነብ ወገኔ አሁኑኑ ተነስተህ በራስህ ላይ ተደርቶ ለእግዚአብሔር እንዳትሰጥ ወደኋላ የሚጐትትህን ሁሉ እግዚአብሔር በየተራ እንዲያነሳልህ ጠይቅ! ከእግዚአብሔርም ተጣበቅ የእግዚአብሔርም ወዳጅ በመሆን የቀረውን የሕይወት ዘመንህን ፈጽም።■

# አሜን!